# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
# *Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*
(ዴሞክራሲያዊ/Democratic)


ጥር ፳፰ ቀን ፪ ሺህ ፩ ዓ. ም
February 5, 2009

## በኢትዮጵያ ውስጥ ስለተከሰተው የሃይማኖት ግጭት የተሰጠ መግለጫ

የኢትዮጵያውያን ተቻችሎና ተፈቃቅዶ የመኖር ምሳሌነታችን በታሪክ የተመዘገበልንና ምስክሮች ቃላቸውን የሰጡበት ሃቅ ነው፡፡ የዚህም ታሪካዊ ክስተት ባለቤቶች አንድ ወጥ የሆን ኢትዮጵያውያን ሳንሆን በብሄር፣ በፆታ፣ በሃይማኖትና በመደብ የተከፋፈልን ኢትዮጵያውያን ነን፡፡ ይህም ክፍፍል ሳይገድበን በችግርም ጊዜ ይሁን በደስታ፣ በክፉ ቀን ይሁን በደግ ጊዜያት በሚያስተሳስሩን የአንድነታችንና የዜግነት ግዴታችን ጉዳዮች ላይ አብረን በጋራ የቆምንበትንና የምንቆምበትን ሰንደቅ ስናስታውስ በኩራትና በመተማመን መንፈስ ነው፡፡

ሆኖም፣ ይህ አዎንታዊ ታሪካችን ብቻውን ሙሉ ታሪካችንን አያካትትም፡፡ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች አንዳንዴ በገዥው ክፍሎች “በኢትዮጵያ የሚገኙ እስላሞች” እየተባሉ እንደ ባይተዋርና ሁለተኛ ዜጋ የተጠሩበትን፣ የዜግነት መብቶቻቸው ተረግጠው በመሬት ስሪት አድልዖ ይሁን በሥራ ዕድል መነፈግና የተያያዙ ሌሎች በደሎች ይደርሱባቸው እንደነበረ የቅርብ ጊዜ ትዝታዎቻችን ናቸው፡፡ ሆኖም ግን፣ በ66ቱ የአብዮት ወቅት፣ ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ታላቅ የብሶት መግለጫ ሰላማዊ ሰልፍ ሲያደርጉ፣ ክርስቲያን ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው አብረው በመሰለፍ ድጋፍ ከመስጠታቸውም አልፈው ለበደሎቹና ሊከተሉ ለሚችሉ ቸግሮች የጋራ መፍትሄ በመሻቱ እንቅስቃሴ ላይ ግምባር ቀደም ሆነው ተሰልፈዋል፡፡ የ66ቱ አብዮት ከሞላ ጎደል በሃይማኖቶች መካከል ያሉትን አድሎአዊ ልዩነቶችን ቀንሷል፣ ለኢትዮጵያውያን የዜግነት መብቶች እኩልነት በጎ አስተዋፅኦ አድርጓል፣ ታሪካዊ መተሳሰሩ ይበልጥ እንዲጎለብትም ረድቷል፡፡

ህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ ወደ ሥልጣን ከመጣ ወዲህ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በሃይማኖቶች መካከልና በእያንዳንዱ ሃይማኖት ውስጥ መጠነ ሰፊ የሆነ ችግር ፈጥሯል፡፡ የኦርቶዶክስ ክርስቲያን ሃይማኖትን ብንወስድ ህጋዊውን ፓትርያርክ ከሥልጣን በማንሳትና ከሲኖዶ ህግጋት ውጭ ሌላ ፓትርያርክ መሾሙ የዚህችን ቤተክርስቲያን ምእመናን ከፋፍሏል፣ አስቆጥቷል፡፡ በአስልምና ሃይማኖት ውስጥም መንግሥት ጣልቃ እየገባ ፖለቲካዊ አመራር ለመስጠት ሞክሯል፡፡ የህወሓት ፖለቲካዊ ምህዋር ክፍፍልንና ልዩነትን በሕዝብ መሀል ማስፋት እንጂ ኅብረትንና አንድነትን ማጉላት አይደለም፡፡ ይህ የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት አንዳንድ ማኅበራዊና ባህላዊ ቅራኔዎች በተዘዋዋሪ መንገድ ወደ ሕዝብ እንዲወርዱና በኅብረተሰባችን ውስጥ እንዲሰረርፁ እያደረገ ነው፡፡ የጎሳና የሃይማኖት ልዩነቶችና ጥላቻዎች በሀገራችን ውስጥ እንዲስፋፉ እየገፋ ነው፡፡ በዚህም ይህ የህወሓት መንግሥት ግጭቶችን ከማብረድ ይልቅ በመቅስቀስና በማፋፋም ሕዝባችንን ወደ ክፉ አደጋና ሊያባራ ወደማይችል የጦርነት አውድማ እየመራ ይገኛል፡፡

ለዚህ የሃይማኖት ግጭቶች መነሳት የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት ከሚፈጥራቸው ምክንያቶች በተጨማሪ ዓለምአቀፋዊ ገፅታ ያላቸው አንዳንድ ምክንያቶችም እንደሚኖሩ መገንዘቡ አስፈላጊ ነው፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንዱ ግሎባላይዜሽን የተባለውና ዓለምን እንደ አንድ አገር እያጠበበ የመጣው ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ክስተት ነው፡፡ ይህ ክስተት በተለይ በድሃ አገሮች ላይ እያደረሰው ያለው የኢኮኖሚና የባህል ምስቅልቅል ከፍተኛ ነው፡፡ ሕዝቦች ከታሪካቸውና ከባህላቸው የተራረፉቸውን ከዚሁ ዓለም አቀፍ ግፊት ለመከላከልና ለመጠበቅ አንዱ እንደ መሣሪያ እየተጠቀሙ ያሉበት ሃይማኖታቸውን ማጥበቅ ነው፡፡ ይህ በራሱ ብቻ ቢሆን ባልከፋ፡፡ ነገር ግን፣ የግል ሃይማኖት እምነቶችን በመለጠጥ፣ ተቻችለው ሲኖሩ የነበሩትን እምነቶች በመጋፋትና በአጥፊና በጠፊነት ከልለው ወደመጨራረሱ እየተጓዙ ነው፡፡ የእምነት ትርጉሞችን በመለጠጥ በአንድ ሃይማኖት ውስጥ ባሉ ተከታዮች መካከል እንኳን ልዩነቶችንና መናቆርን እያስፋፉ ናቸው፡፡

*ሀገራችንም የዚህ ክስተት ተቋዳሽ መሆኗ አልቀረም፡፡ ሆኖም ግን፤ በነዚህ ውስጣዊና ውጫዊ ግፊቶች ምክንያት ሙላላትና መገዳደል ተከባብሮና ተጋግዞ ከኖረው ከኢትዮጵያዊ ዜጋ የሚጠበቅ አይደለም፡፡*

*የማያሻሙ የዜግነት ግዴታዎች አሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ ዋነኛው በመደብ፤ በሃይማኖትና በብሄር በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ ዜጎች በሚያስሟሟቸው ብሄራዊ ጉዳዮች ላይ ስምምነት አድርገው ሃይማኖታቸውን በግል ይዘው የሌሎችን ሃይማኖት አክብረው በጋራ አገራቸውን መገንባትና ለተሻለ ቀን በጋራ መታገል ነው፡፡ ይህ የዜግነት ግዴታ የሃይማኖት አባቶችና መሥራቾች ካስተማሯቸዉ መሠረታዊ የመቻቻል ትምህርቶች ጋር ይስማማሉ፡፡*

*ነቢዩ መሐመድ ዘመዶቻቸውንና ተከታዮቻቸውን ወደ ኢትዮጵያ እንዲሰደዱ አዘው ሀገራችንም በደረሱ ጊዜ ተከታዮቻቸውን ተቀብላ አክብራ ያኖረቻቸውን ኢትዮጵያ "የክርስቲያን ደሴት" ናት ማለት አግባብ አይኖረውም፡፡ ለኢትዮጵያ ሙስሊሞችና ለሌሎች ሃይማኖት ተከታዮች ቦታ የሚነፍግ አገላለፅ ነው፡፡ "ሃይማኖት የግል ሀገር የጋራ ነው" የሚለውን መሠረታዊ መርህ ይቃረናል፡፡ ዛሬ "መስኪድ ብዙ ተሠራ፤ ቤተክርስቲያን የተሠራው በሙስሊሞች ቦታ ላይ ነው…ወዘተ" በሚል መዘባራት አያምርብንም፤ ከማንም ሆነ ከየትም ይምጣ አስተሳሰቡም ሆነ አባባሉ አደገኛ ነው፡፡*

*ባለፈው ዓመት በጅማና በአካባቢው በሚያሳፍርና በሚዘገንን ሁኔታ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች የተሳለቁበትን አደገኛ ክስተት አይተናል፡፡ ያ እልቂት ሳያንስ፤ ዛሬ ቂም ለመቀስቀስ ሲሉ የዚያን ቪዲዮ እየተለዋወጡ የሚገኙ በሁለቱም ሃማኖቶች ስም የሚምሉና የሚገዘቱ ጥቂት ተወናብደው የሚያወናብዱ ተከታዮች ሌላ የጂማን እኩይ ተግባር ለማምጣት የሚያደርጉት ሙከራ እንዳለ እንገነዘባለን፡፡ ይህ መወገዝ ያለበት ሰይጣናዊ እቅድ ነው ብለን እናምናለን፡፡ በኢትዮጵያዊ ጭንቅላት ጨርሶ ሊታሰብ የማይገባው ሀገርንና ሕዝብን በቁም የሚቀብር አደገኛ አስተሳሰብና አካሄድ መሆኑን ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ሊያስገነዝብ ይሻል፡፡ ሁሉም በአንድ ተዳምሮ ነው እንጂ በሁለቱም በኩል ካሉት አማንያን መካከል በጣም ምሳሌያዊ የሆኑ የመቻቻል አርአያዎች ቁጥራቸው አያሌ እንደሆነም ለማስገንዘብ እንወዳለን፡፡ የነዚህ ንፁህ ዜጎች ድምፅ በጥቂት አክራሪዎች ጩኸት እንዳይዋጥ ለማሳሰብ የምናደርገው ጥረት ዛሬም ሆነ ወደፊት ባመቸው የመገናኛ ዘዴ ሁሉ ይቀጥላል፡፡*

*በዚህ አጋጣሚ ይህን የሃይማኖት ውዝግብ ለማርገብና በጋራ በኢትዮጵያዊነት ስሜትና መግ ባባት እንድንኖር ለማደረግ የበለጠ ሃላፊነቱን የሃይማኖት አባቶችና መሪዎች ትልቁንና ዋነኛውን ድርሻ ይሸከማሉ፡፡ ስለዚህም ከትውልድ ትውልድ ሲወርድና ሲዋረድ የኖረው የኅብረተሰቡ ፍቅርና ግንኙነት ይበልጥ የሚዳብርበትን መንገድ በመቀየስ አሁንም ላሉት ሆነ ወደፊት ለሚፈጠሩት ችግሮች በጋራ በውይይት እንዲፈቱ አጥብቀን እናሳስባለን፡፡*

*ሃይማኖቶች የመቻቻልና አብሮ የመኖር አርአያ ናቸው!!*
*ኢትዮጵያ የሃይማኖቶች እኩልነትና መቻቻል ምሳሌ መሆኗን ትቀጥላለች!!*

**850 Sligo Avenue Suite # 8** **P.O.Box 8141** **P.O.Box 88675**
**Siver Spring , MD 20910** **Silver Spring, MD 20910** **Los Angeles, CA 90009**

**Phone: 301-578-4466** **Fax: 301-449-8363** **Email Address**: **eprp-democratic@eprp-ihapa.com**